★ዴሞክራሲያ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ዴሞክራሲያ ቅጽ** 35 **ቁጥር** 6 **ግንቦት** 2002 **ዓ.ም**


## <u>እውነተኛ ምርጫ በሕዝብ ትግል እውን ይሆናል</u>

*ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በየአምስት ዓመቱ እየተደጋገመ የሚታየው አሰልቺ የሆነው የምርጫ ትርዒት ዘንድሮም ይበልጥ አሰልቺ በሆነ መንገድ እየታየ ነው፡፡ በመጭው ግንቦት* 15 *ቀን* 2002 *ዓ.ም የመጨረሻው ትዕይንት የሚታይበት የምርጫው ድራማ ተውኔቶቹ መታየት ከጀመሩ ጥቂት ቀናት ሆኗቸዋል፡፡ የቲያትሩ ዋና ተዋንያን የሆኑና ከ*60 *በላይ የወያኔ ተለጣፊዎች የሚገኙባቸው* 63 *ፓርቲዎች ለመወዳደር ተመዝግበዋል ተብሏል፡፡* 6938 *የሚሆኑ ግለሰቦችም ለፌዴራልና ለክልል ምክር ቤት እንደሚወዳደሩ ተገልጿል፡፡ ለምርጫው ቲያትር* 149.5 *ሚሊዮን ብር መመደቡ እንዲሁም ከ*43*ሺ በላይ የሆኑ የምርጫ ጣቢያዎችን የሚያስተናግዱ አብዛኞቹ የወያኔ አባላት መሆናቸው የተረጋገጠ* 220 *ሺ በላይ የምርጫ አስፈጻሚዎች መሾማቸው ታውቋል፡፡ ተቃዋሚ ነን ከሚሉ አንዳንድ ድርጅቶች ጋር ወያኔ የምርጫ ሥነ ሥርዓት ስምምነት ተፈራረምኩ ብሏል፡፡ ተወዳዳሪዎች ዓላማቸውን ለሕዝብ የሚያስረዱበት የሚዲያ/ የመገናኛ ብዙኃን/ ሰዓት ተሰጥቷቸዋል ተብሏል፡፡ በቴሌቪዥን አማካይነትም በየቀኑ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የምርጫ ክርክር ተደረገ ተብሎ ይደለቃል፤ ተቃዋሚዎች ሕዝብ ሰብስበው የምረጡኝ ዘመቻ እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸዋል፤ ከውጭ ታዛቢዎች ተጋብዘዋል፥ ከውስጥም ተመድበዋል ተብሏል፡፡ ተውኔቶቹ በየተራ በየቀኑ እየታዩ ቢሆንም፥ ላለፉት* 20 *ዓመታት በተደጋጋሚ ታይተው ሕዝብን ያሰለቹ በመሆናቸው ተመልካች አላገኙም፡፡ ሆያ ሆዬውና ዘፈኑም በወያኔ ዙሪያ ሆኖ ብቻ ተወስኖ የቀረ መሆኑ ይታያል፡፡*

*አምባገነን አገዛዞች በየወቅቱ ምርጫ ምርጫ እያሉ የሚያሰለቹን የይስሙላ ምርጫ ባህሪዎቻቸውንና ተግባሮቻቸውን ለመሸፈን የሚጠቀሙበት ዘመናዊ ስልት በመሆኑ ነው፡፡ የመንግሥቱ ኃይለማርያም የምርጫ ቲያትር፤ የእነ ኦማር አል በሽር በሱዳንና የእነ ሙጋቤም በዚምባብዌ የይስሙላ ምርጫዎች እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ወያኔም ባለፉት* 20 *ዓመታት ተደጋጋሚ የይስሙላ ምርጫዎች አካሂዶ የዴሞክራሲያዊነትን ካባ ለመጎናጸፍ ብዙ ባዝኗል፡፡ የተካሄዱት የይስሙላ ምርጫዎች ግን ለወያኔ ጭምብል ከመሆን ይልቅ ይበልጥ ምንነቱን ማንነቱን ያጋለጡት ሆነዋል፡፡ የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መልሶ እንዲሉ አሞኘዋለሁ፥ አታልለዋለሁ የሚለው ክፍል ውሸት መሆኑን አውቀ ነቅቶ*

በሚጠብቀበት ሁኔታ ዘንድሮም አሰልቺ የሆነ የምርጫ ቲያትሩን ለመድገም ላይና ታች እያለ ይገኛል፡፡

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን የሚያረጋግጠው አንዱ መንገድ በምርጫ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በኀብረት ራሱን ለማስተዳደር የወሰነ ሕዝብ ጥቅሜን ይጠብቁልኛል፥ ፍላጎቴን ያሟሉልኛል የሚላቸውን ወኪሎች ወደ ሥልጣን ሊያወጣ የሚችልበት ብቸኛው መንገድምርጫ ነው፡፡ ሕዝብ ሉዓላዊነቱንና የሥልጣን ምንጭነቱን በምርጫ አማካይነት ሊያረጋግጥ የሚችለው ግን በቅድሚያ ነፃነቱ ሲጠበቅለትና መብቱ ሲረጋገጥለት ነው፡፡ ሕዝብ ነፃነቱን የሚቀዳጀው ከውጭ ኃይል ተጽእኖ በመላቀቅ ብቻ ሳይሆን የመንግሥትን ሥልጣን ከተቆጣጠረና ኃይልና ተገን ካደረገ ማንኛውም ወገን ከሚያደርስበት ጭቆና፥ በደል ወይም የኃይል ርምጃም ነፃ ሲሆን ጭምር ነው፡፡ መብቱም የሚጠበቅለት መሠረታዊ የሆኑት የንግግር፥ የመሰብሰብ፥ የመንቀሳቀስ፥ የመደራጀት፥ የፈለገውን የመምረጥ፥ የሃይማኖት፥ ተቃውሞን የማሰማት፥...ወዘተ መብቶቹ አለምንም ገደብ ሲከበሩ ነው፡፡ ሕዝብ በስምምነት ያፀደቀው ሕገ መንግሥትና ሌሎች የሀገሪቷ ሕጎች ሁሉ የበላይነታቸው ተረጋግጦ ሲከበሩና ሕግን የሚያስከብሩ አካሎች ማለትም የፖሊሱ፥ የፀጥታው፥ የወታደሩና፥ የሕግ ሌሎች ተቋማት ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ተደራጅተው፥ ከማንም ግለሰብ ወይም ቡድን ቁጥጥር ነፃ ሆነው ሲቋቋሙ፤ በገለልተኛነት ለሕግ ብቻ ታዛዥ ሆነው ሥራቸውን የሚያካሂዱበት ሁኔታ ሲፈጠር የሕዝቡ ነፃነት ተከብሯል መብቱም ተረጋግጧል ማለት ይቻላል፡፡ ነፃነትና የመብት መረጋገጥ ሥልጣን ከያዘ ኃይል ወይም ግለሰብ መልካም ፈቃድ የሚገኙ ወይም በቸርነት የሚለገሱ አይደሉም፥ የሕዝቡ የትግል ውጤት ናቸው እንጂ፡፡ ሕዝቡ በትግሉ በኅብረትና በስምምነት ዕውን የሚያደርጋቸው፥ ማንም ግለሰብ ወይም ቡድን በምንም ጊዜ በኃይልም ሆነ ሕግ በማውጣት ሊነጥቃቸው የማይችሉ የማይደፈሩና የማይገሰሱ መሠረታዊ መብቶች ናቸው፡፡ ሕዝብ ሉዓላዊነቱን አስጠብቆ የሥልጣን ባለቤትነቱን በምርጫ አማካይነት እውን ሊያደርግ የሚችለው እነዚህ መሠረታዊ መብቶቹ ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ነፃነት፥ መብት፥ ዴሞክራሲና ምርጫ የማይነጣጠሉና የተያያዙ ናቸው፡፡ ነፃነት፥ መብትና ዴሞክራሲ በሌሉበት ምርጫ የአምባገነኖች መሸፈኛ ይሆናል እንጂ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነቱን እውን የሚያደርግበት መሣሪያ አይሆንም፡፡ ምርጫ ከነፃነት፥ ከመብትና ከዴሞክራሲ ውጭ ቃል ከመሆን ያለፈ ትርጉም ሊኖረው አይችልም፡፡ አንድ ፓርቲ ወይም ግለሰብ በምርጫ ቢያሸንፍ እንኳ ፖሊሲውን በተግባር ለማዋል የሚያስችል ዋስትና ካለመኖሩም በላይ በማናቸውም ጊዜ በሕዝብ ሳይሆን ኃይልን በሚቆጣጠረው አምባገነን ቡድን ከሥልጣን ሊነሳ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ምርጫ ብቻውን ነፃነትና ዴሞክራሲ አያመጣም፡፡ የዴሞክራሲ መሠረቶች ካልጠነከሩ አምባገነኖችና ፋሽስቶች በምርጫ ወደ ሥልጣን መጥተው የሕዝቡን መብት ሊያፍኑ፥ ነፃነቱን ሊያግዱ ይችላሉ፡፡ ሒትለር፥ ሙሶሎኒ እና ሌሎች አምባገነኖች ወደ ሥልጣን የመጡት በምርጫ መሆኑን መገንዘብ ይጠቅማል፡፡

ከላይ የተገለጹት መሠረታዊ የሕዝብ መብቶቹ ተከብረውና የሕዝቡ ነፃነቶች ተጠብቀው እንኳ የተጭበረበረ ምርጫ ሊካሄድ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል። የተሟላ፥ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ ምርጫን ለማካሄድ የግድ የምርጫው ውድድር በተስተካከለና ለሁሉም በእኩልነት በሚያገለግል ሁኔታ ላይ መደረግ ይኖርበታል። ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሊካሄድ የሚችለው ለሁሉም ተወዳዳሪዎች በዕኩልነትናበገለልተኛነት አገልግሎት የሚሰጥና በአንድ ፓርቲ ሳይሆን በተወዳዳሪ ፓርቲዎች የጋራ ውሳኔና ስምምነት የሚቋቋም የምርጫ አስፈጻሚ አካል ሲኖር፤ ለሁሉም ወገን በዕኩልነት የሚያገለግል የምርጫ ሕግና የሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ደንብ ሲደነገግና በሥራ ላይ ሲውል፤ ሕዝቡ የመምረጥና በምስጢር ድምፅ የመስጠት መብቱ ሲከበር፤ ተወዳዳሪዎች እኩል የሆነ የሚዲያ (የመገናኛ ብዙሀን) ሰዓት ሲያገኙ፤ ለምረጡኝ እንቅስቃሴው እኩል ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብና ሌሎች አገልግሎቶች ሲመደቡ፤ የምርጫ ጣቢያዎች እኩል በሆነ ደረጃ ለሁሉም ሲዳረሱ፤ የምርጫ አካሎችም አለ አድልዎ በዕኩልነት ሁሉንም ተወዳዳሪ ሲያስተናግዱ፤ የፀጥታ ኃይሎች ከማስፈራራትና ከጣልቃ ገብነት ሲቆጠቡ፤ የድምፅ ካርዶች በአግባቡ ሲሰበሰቡና ሲቆጠሩ፤ ነፃና ገለልተኛ የሆኑ ታዛቢዎች አለምንምገደብ የምርጫውን ሂደት እንዲታዘቡ ሲደረግ እና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው።

ሀገራችን ውስጥ ሁለቱም ሁኔታዎች የተሟሉ አይደለም - ሕዝብ ነፃነቱን ተገፏል፥ መብቱም የተከበረ አይደለም። የሕግ አስከባሪ አካሎችና የመንግሥት የመጨቆኛ መሣሪያዎች በወያኔው ድርጅት ቁጥጥር ብቻ ሳይሆን በባለቤትነት የተያዙ ናቸው። ወታደሩ፥ የፀጥታው ክፍል፥ የፖሊስ ኃይሉ፥ ቢሮክራሲው፥ የግል ወታደራዊ ተቋማት (ፌዴራል ፖሊስ፥ አግዓዚ የቀበሌና የገበሬ ማህበራት ታጣቂዎች)፥ የፍርዱ ተቋማት ሙሉ በሙሉ በወያኔ ቁጥጥር ሥር፥ ውስጥ ነው ያሉት። በወያኔ ቁንጮ ተሹመው በወያኔ ፓርላማ ሹመታችው ፀድቆ ኃላፊነት የተሰጣቸው የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የመረጣቸውን ጌታ ብቻ ሲያገለግሉ የቆዩ አሁንም እያገለገሉ ያሉ ናቸው። የምርጫ ሕጉ ወያኔን ብቻ እንዲያገለግል ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ የዋለ ነው። ወትሮም በብዙ ችግርና መከራ ይንቀሳቀስ የነበረ ነፃ ፕሬስና ሚዲያ (መገናኚያ ብዙኃን) እስከናካቴው ከታፈነ ዓመታት አልፈዋል። አፋኝ በሆኑ ሕጎች አማካይነት የሲቪል ድርጅቶችና ሌሎች ነፃና ገለልተኛ አካሎች ምርጫው ነፃና ፍትሐዊ መሆኑን እንዳይከታተሉና እንዳይታዘቡ ለማድረግ ተሞክሯል። በርካታ ሰላዮች ተቀጥረዋል፥ የስለላ መሳሪያዎች በየመንገዱ ተሰቅለዋል። በምርጫ ወቅት የኃይል ተጽዕኖ የሚያደርጉና የአፈና ተግባራትን የሚያከናውኑ ልዩ ልዩ የሆኑ ወታደራዊ ተቋማት ተመሥርተው ሥራቸውን ለመጀመር እየተጠባበቁ ነው። ይህምብቻ አይደለም-- ሌሎች የማስፈራሪያና የመደለያ ስልቶችም በሥራ ላይ ውለዋል። በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፥ በትምህርት ቤቶች፥ በጤና ተቋሞች፥ በፋብሪካዎች፥ በአገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የሚሠሩ ሠራተኞች፥ በየገጠሩ ያሉ አርሶ አደሮች ኢሕአዴግን ምረጡ እየተባሉ ቀጥተኛም ሆነ የተዘዋዋሪ ተጽእኖ ተደርጎባቸዋል ፤ አሁንም

እየተደረገባቸው ነው። በሚሊዮን የሚቆጠሩ በግድ የኢሕአዴግ ፓርቲ አባል ሁኑ ተብለው ተደርገዋል። ኢሕአዴግን ከመረጣችሁ ሥራና ሹመት እንዲሁም ገንዘብ ታገኛላችሁ የሚለው መደለያ ለብዙዎቹ ቀርቧል። ባለፈው ምርጫ ማን ለማን እንደመረጠ መረጃ አለን አሁንም ከኢሕአዴግ ውጭ የሚመርጥ ወዮለት የሚል ማስፈራሪያ ለተቃዋሚ ደጋፊዎች እንዲደርስ ተደርጓል። ለዚህም ነው እንደ ደርግ ጊዜው ዛሬም የዚህ አካባቢ ተማሪዎች፥ የዚህ አካባቢ ሠራኞች፥ የዚህ አካባቢ ገበሬዎች፥...ወዘተ ተሰብስበው ኢሕዴግን ለመምረጥ ውሳኔ አስተላለፉ፥ ማሉ ተገዘቱ የሚል ዜና በተለያዩ ሚዲያዎች መሰማታቸው ብዙዎችን ያላስደነቀው። የግል ምርጫን ለማካሄድ በቡድን ውሳኔ እየተደረገ ነው። በፍርሃት አየር ውስጥ በአፈና ታጅቦ የሚካሄድ ምርጫ የሕዝብ ሉዓላዊነትን በተግባር የሚያውል እውነተኛ ምርጫ ሊሆን አይችልም፤ ለይስሙላ የሚደረግና አስመሳይ ምርጫ እንጂ። ሐቁ ሲገለፅ ግን ብዙኀኑ ለምርጫ አልተመዘገበም--ወያኔ 29 ሚሊዮን ተመዝግቧል ብሎ ቢዋሽም። እንዳለፉት ጊዜያቶች ሁሉ አዳናቂው ቢበዛ፥ የአየር ሞገዱ ቢጨናነቅና፥ ሆይ ሆይ የሚለውም እንደጎርፍ ቢጥለቀለቅ የዘንድሮውም የወያኔ ምርጫ ያው ደጋግሞ የታየው አሰልቺ ቧልት መሆኑ ግልጽ ነው። አሸናፊዎቹ የቲያትሩ መሪ ተዋንያን መለስና ፓርቲው መሆናቸው ሳይታለም የተፈታ ነው። በወያኔ አገዛዝ በምንም ተአምር እውነተኛ ምርጫ ሊካሄድ የማይችል መሆኑን ደጋግመን የገለጽነው ነው።

አንዳንዶቹ የተበላ እቁብ የሚል ስም የሰጡት መጭው የወያኔ የይስሙላ ምርጫ በወያኔ አሸናፊነት የሚጠናቀቅ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ ከምርጫው አንድ ዓይነት ቁም ነገር ይገኛል በሚል ሕዝብን ለማዘናጋት በውስጥም ሆነ በወጭ ወዲያና ወዲህ የሚሉ ክፍሎች ቁጥራቸው በርካታ መሆናቸው ባያስገርምም ውዥንብሮቹና፥ የማደናገሪያው ዘዴዎቹ አይነታቸው እየተበራከተ መምጣቱ አነጋጋሪ ሆኗል። ደግነቱ በደም ከከፈለው ተመክሮ በመነሳት አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫው ፍትሐዊነትና ነፃ መሆን ላይ ቅንጣት ታህል እንኳ እምነት የሌለው በመሆኑ በእነዚህ ወገኖች እየተስፋፉ ያሉ አመለካከቶች ሕዝብን በማወናበድ በኩል ውጤት አልባ መሆናቸው ከወዲሁ እየታየ ነው። የወያኔ ተለጣፊ የሆኑ፥ ከወያኔ ፍርፋሪ የሚያገኙ፥ ከራሳቸው ጥቅም በስተቀር የሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ቅንጣት ታህል የማያሳስባቸው በተደጋጋሚ ምርጫ ውስጥ ገብተው ለወያኔ የዴሞክራሲያዊነት ካባ ሽፋን ሲሰጡ የቆዩ በመሆናቸው ዘንድሮም ይህንኑ ሲደግሙ ቢታዩ ብዙ የሚያስገርም አይደለም። እነዚህ ክፍሎች ምን ጊዜም የሚያስቀድሙት የግል ጥቅማቸውንና ምቾታቸውን እንጂ ሕዝብን ስላልሆነ በተደጋጋሚ የታየው አቋማቸው ሆነ ድርጊታቸው አስገራሚ ሊሆን አይችልም።

እንዲሁም ጥቅማቸውን ብቻ የሚመለከቱ የባዕዳን መንግሥታትም የኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ነፃነት አልባ መሆኑንና ምርጫው የዓለም አቀፍ የምርጫ ሂደት መመዘኛን አለማሟላቱን እያወቁ ለአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ቢሰጡ፥ የምርጫውን ትክክለኛነት ለማጽደቅ ታዛቢዎች ልከናል ቢሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ብዙ የሚያስገርመውና የሚያስደንቀው ከቶ

አይደለም:: የባዕዳን ኃይሎች፥ በተለይም በምዕራብ ያሉ መንግሥታት የእምነታችን ዋልታዎች ናቸው የሚሏቸው፥ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ፥ የሕግ የበላይነት መኖር፥ የነፃና ፍትሐዊ ምርጫ እውን መሆን፥...ወዘተ በሌሎች አገሮች ተግባራዊ ሆኑ አልሆኑ ብዙ ሲያስጨንቃቸው አላየንም:: በየአካባቢው ላሉት ሁኔታዎች የሚሰጡት መልስና የሚወስዱት እርምጃ ከጥቅማቸው አንጻር ብቻ መሆኑን ከተረዳን ውለን አድረናል:: ጥቅማችውን ለሚያሰጠብቁላቸው አምባገነኖች በቢሊዮን የሚቆጠር የገንዘብና የሌሎች ቁሳቁሶች እርዳታና ዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ እየሰጡ በሥልጣን እንዲቆዩ የሚችሉትን ጥረት ያደርጋሉ:: በእነዚህ አገሮች ለሚደረጉ የሰብዓዊ መብቶች ረገጣዎች አፈናዎች፥ ወይም በምርጫ ወቅት ለሚደረጉ ጭፍን የሆኑ ማጭበርበሮችና ተያይዘው ለሚመጡ ወከባዎችና ግድያዎች ከአንገት በላይ የሆኑና ጥርስ የሌላቸው የተቃውሞ መግለጫዎችን ከማውጣት ባሻገር ተጨባጭ እርምጃዎችን ሲወስዱ አልታዩም:: በሌላ በኩል እንደነ የዚምባቤው ሙጋቤ የመሳሰሉትና ለምዕራብ አገሮች ጥቅም ተፃራሪ ናቸው ተብለው የተፈረጁ አምባገነኖች በየአገሮቻቸው ምርጫ አጭበርብረዋል በሚል ወገዛ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ማዕቀብ በማድረግ ሆነ የወታደራዊ እርምጃ ጥቃት ሲቃጡባቸው አስተውለናል:: ወያኔን ተረባርበው ወደ ሥልጣን ያወጡት ምዕራባውያን ናቸው፤ በየዓመቱ በአማካይ አንድ ቢሊዮን ዶላር በመስጠት፥ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ሥልጣን ላይ እንዲቆይ አድርገውታል:: ባንጻሩ ወያኔ የምዕራባውያን ጥቅም አስጠባቂ ነው:: ስለሆነም ወያኔ ለሚያደርገው የሰብዓዊ መብት ረገጣ የፍትሕና የሰብዓዊ መብት እጦት ባዕዳን ኃይሎች የአንገት በላይ ጩኸት ቢያሰሙና የወያኔ ምርጫ የይስሙላ መሆኑን እያወቁ ታዛቢ በመላክ ሆነ በሌሎች ተግባሮች ላይ ትብብርቢያሳዩ የሚያስገርም አይደለም::

ሰልፋቸው ከተቃዋሚ ኃይሎች ሆኖ በተአምር ምርጫውን በአሸናፊነት እናጠናቅቃለን የሚሉ የዋሃን ካሉ ለእነዚህ ወገኖች ማስተላለፍ የምንፈልገው መልዕክት እስካሁን ያለፈንበት ችግርና የከፈልነው መስዋዕትነት ትምህርት ሊሰጠን ይገባልና አሁንም ከዚህ እንማር የሚል ነው:: ምርጫውን በምንም ዓይነት መንገድ ማሸነፍ እንደማይቻል በየአደባባዩ እያስረገጡ፥ ባጭር ጊዜም ሆነ በረዥም ጊዜ ከምርጫው ጥሩ ውጤት ማግኘት ይቻላል ለሚሉት ወገኖች፤ ይህ አያዋጣም እንላቸዋለን:: በምርጫው ወያኔ ይጋለጥበታል፥ ወያኔን በዘንድሮ ምርጫ ማሸነፍ ባይቻልም የዛሬ አምስት ዓመት ወይም የዛሬ አሥር ዓመት የማሸነፉን ሁኔታ ማመቻቸት ይቻላል፤ ሕዝቡን በህቡዕ ሆነ በይፋ ማደራጀት የሚቻለው በምርጫ መሳተፍ ሲቻል ነው፤ ሕዝቡ መሪ ይፈልጋልና በምርጫ ካልተሳተፉ ሕዝቡን መምራት አይቻልም፥ አብላጫ ድምፅ አግኝተን የመንግሥቱን ሥልጣን መያዝ ባንችልም በወያኔ ፓርላማ ጥቂት መቀመጫዎችን አግኝተን ወያኔን ልናጋልጥ የምንችልበት ሁኔታ ይኖራል፤... የሚሉት አመለካከቶች ሁሉ ደግነቱ ሕዝቡ በራሱ ተመክሮ ስለምርጫው ዋጋ ቢስነት ቀድሞ ሁሉንም ነገር ተገንዝቦ መጥቀ ሂዷል እንጂ አደናጋሪ ሊሆኑ በቻሉ ነበር::

በአጭበርባሪነቱ፥ በመሠሪነቱና በፈላጭ ቆራጭነቱ ግልጥጥ ብሎ የወጣ ቡድንን በይስሙላው ምርጫተባባሪ በመሆን በምን ዓይነት መንገድ በአዲስ መልክ ማጋለጥ እንደሚቻል ሊገባን

አልቻለም። አጭበርባሪነቱን በሚገባ ለሚያውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያመጣው ፋይዳ የለም። ባዕዳንም እስካሁን የተደረጉት ምርጫዎች ነፃና ፍትሐዊ አለመሆናቸውን እያወቁ ስለሆነ ወያኔን ሲደግፉ የቆዩት የማጋለጡ ጥረት ከባዕዳኑ አንጻር ብዙ የሚፈይደው ነገር የለም። በምርጫ ከተሳተፍን በአሁኑ ምርጫ ባይሳካ እንኳ በሚቀጥሉት 10 እና 15 ወይም 20 ዓመታት ማሸነፍ እንችላለን የሚለው የመከራከሪያህሳብ ውሃ የሚቋጥር አይደለም። የወያኔው ቡድን ስልቱን እየለዋወጠና እያሻሻለ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ይጥራል እንጂ ዝም ብሎ አይቀመጥም። ካለፈው ምርጫ ወዲህ የወያኔ ቡድን በአንድ በኩል ራሱን በሥልጣን ለማቆየት በሌላ በኩል ተቃዋሚዎችን ለመከፋፈልና ለማዳከም በወሰዳቸው እርምጃዎች የተነሳ ሁኔታው በይበልጥ ለዚህ ቡድን አስተማማኝ እየሆነ መምጣቱን አይተናል። ባሁኑ ወቅት ማሸነፍ ካልተቻለ በምን ተአምር የዛሬ 5፥ 10 እና 20 ዓመት ማሸነፍ እንደሚቻል ግልጽ አይደለም። ሕዝቡ መሪ እንደሚፈልግ ግልጽ ነው፣ በግንዛቤ መጥቆ ሄዷል፣ ምን መደረግ እንዳለበትም ያውቃል፣ አስተባባሪና መሪ ይፈልጋል። የሕዝብ መሪ ለመሆን ግን የግድ በአለቀለት ምርጫ ተሳታፊ መሆንን አይጠይቅም። እንዲያውም ለሕዝቡ ያልሆነ ተስፋ፥ ለአምባገነኖች ደግሞ የዴሞክራሲያዊነት ሽፋን በመስጠት የሕዝቡን ትግል ያዳክማል። በወያኔ ፓርላማ ውስጥ ገብቶ ወያኔን እያጋለጡ ቀስ በቀስ ኃይሉን መሸርሸር የሚለውም የማይጨበጥ ተስፋ ነው። ከወያኔ ፍላጎት ውጭ ተጨባጭ ሥራዎችን በማይሠራ ፓርላማ ውስጥ ተቃዋሚ ሆኖ መሰየም ወያኔ የሌለውን የቆዳ ቀለም ለራሱ እየሰጠ ከማንኛውም የበለጠ ዴሞክራሲያዊ ነኝ የሚለውን መመጻደቂያ አድርጎ ሲጠቀመበት ታየ እንጂ ሲጋለጥበት ወይም ኃይሉ እየመነመነ ሲመጣ አልታየም።

ታዲያ መፍትሔው ምንድን ነው? ሕዝቡስ ከዚህ መከራና ስቃይ እንዴት ነው ሊላቀቅ የሚችለው የሚለው ጥያቄ አግባብነት ያለው ስለሆነ በተገቢው መንገድ መመለስ ያለበት ነው። ከዚህ ቀደም ደጋግመን እንደገለጽነው አምባገነን ኃይሎች የዘረጉት የአፈናና የጭቆና ሥርዓት ሊወገድ የሚችለውበሕዝብ ኃይልና ግፊት ብቻ እንጂ በልመና ወይም እነዚህ አጥፊ ኃይሎች በዘረጉት ወጥመድ ውስጥ ገብቶ በመዋኘት አይደለም። የትግሉ ስልት ሰላማዊና ሰላማዊ ያልሆኑ መንገዶችን ሊከተል የሚችልመሆኑ ግልጽ ሲሆን ከሁለቱ አንደኛውን የመምረጥም ሆነ እንደሁኔታው ሁለቱንም አብሮ በማስኬድየመታገልና ትግሉን ግብ የማድረስ መብት የሕዝብ ነው። የትኛውም የትግል ስልት ተመረጠ ትግሉን ለማካሄድም ሆነ በድል ለማጠናቀቅ በቅድሚያ መደራጀትን ይጠይቃል። እስከ አፍንጫው የታጠቀውንና በባዕዳን ኃያላት እየተረዳ ያለውን አምባገነን ኃይል ታግሎ ማሸነፍ የሚቻለው ሕዝቡ ማለቂያ የሌለውን ጉልበቱንና ኃይሉን አስተባብሮ ሥልጣኑን በጨበጠው ፀረ ኢትዮጵያ ቡድን ላይ ምቱንሲያሳርፍ ብቻ ነው። ስለሆነም መደራጀት ጊዜና ቦታ የማይጠይቅ የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው። በወያኔ የይስሙላ ሕግ ተጠቅሞ በይፋ መደራጀት የሚቻል ቢሆንም እዚህ ላይ ክብደት ሰጥተን የምናነሳው በህቡዕ የመደራጀትን ወይም የትግል ተግባርን በህቡዕ የማካሄድ ሁኔታን ነው። የአምባገነኑ የፀጥታ ኃይሎች በተጠናከሩበት ወይም ሰላይና ሰርጎ-ገቡ

በብዛት በሚርመሰመስበት ሁኔታ በይፋ ሳይሆን በህቡዕ መደራጀቱና ተግባርን በህቡዕ ማካሄዱ ለትግሉም ሆነ ለውጤቱ አስፈላጊ ነው፡፡ በህቡዕ የተደራጀና ለትግል የቆረጠ ሕዝብ ኃይል፥ በልዩ ልዩ ምክንያት የተለያየ ዘዴ ስልት በመጠቀም በሥልጣን ላይ ያለውን ኃይል ሊያስወግድ ይችላል፡፡ ቀድሞ የሶቭየት ግዛት በነበረችው ኪርግስታን በህቡዕ የተደራጀ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የታጠቀን አምባገነን ኃይል ከሥልጣን ሲመነግል ለማየት ችለናል፡፡ በኔፓልና በምዕራብ አፍሪካ፥...ወዘተ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች አምባገነን ኃይሎችን ሲያርበደብዱም ተመልክተናል፡፡ በ1997 ምርጫ ገንፍሎ የወጣው የሕዝብ ቁጣና ምሬት የተደራጀ መልክ ኖሮት ቢሆንና ይህም እንቅስቃሴ ለሕዝብ ጥቅም በቆመ የተደራጀ ኃይል ተመርቶ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የሕዝቡ ትግል ግቡን መትቶ አምባገነን አገዛዝ ተወግዶ የምናይበት ወቅት ላይ እንሆን ነበር፡፡ ሕዝብእንደማዕበል ከተነሳ ምንም የሚያግደው ኃይል አይኖርም፡፡ በአግዓዚ ሆነ በፌዴራል በሕወሓት ሆነ በኢሕአዴግ ስም እስካፍንጫቸው ታጥቀው አምባገነኑን የሚያገለለግሉ ወገኖች የሕዝብ ቁጣና እንቅስቃሴ እንደማዕበል ገንፍሎ ሲወጣ ሰልፋቸው ከሕዝብ ጎን እንዲሚሆን አሊያም ሽንፈትን እንደሚከናነቡ ምንም ጥርጥር ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም ተደራጅቶ መታገል አሁንም የወቅቱ ዓቢይ መፈክር ነው፡፡

ለሕዝብ የቆሙ እውነተኛ ተቃዋሚ ኃይሎች ሕዝብን ለትግል ሊያበቃ የሚስችል ድርጅታዊ ሥራናእንቅስቃሴ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ታጋዩ ሕዝብም አገሩን ከስቃይ ለማውጣት ትግሉን መርተው ከግቡ ሊያደርሱ ይቸላሉ የሚላቸውን ድርጅቶች መርጦ የመቀላቀልና የመታገል ግዴታ አለበት፡፡ ኢሕአፓ ለሕዝብ የገባውን ቃል ኪዳን ለአንዲት ደቂቃ እንኳ ሳይጥፍ ከፍተኛ መስዋዕትነትን እየከፈለ በከተማም ሆነ በገጠር ሕዝብን እያደራጀና ትግሉን እያፋፋመ ይገኛል፡፡ ታጋይ ኃይሎች በድርጅቱ ጥላ ሥር ተሰልፈው ሕዝባዊውን ትግል እንዲያካሂዱ አሁንም ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡ ከሚስጥራዊነቱ የተነሳ በድርጅቱ ውስጥ መታቀፍ አስቸጋሪ ቢሆን እንኳ ከሚያምኑትና ከሚመስለው ጋር እየመከሩ በመንፈስ ተዘጋጅቶ መጠበቅ የቁርጧ ቀን ለት ኃይልን አስተባብሮ፥ ከታጋይ ኃይሎች ጋር ተሰልፎ አምባገነኑን ለማስወገድ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ይቻላል፡፡

ስለሆነም የሀገር ፍቅር የሚያንገበግበው ሁሉ ዛሬውኑ ተጨባጭ እርምጃ ይውሰድ፤ መፍትሔው ትግል ብቻ ስለሆነ ተደራጅቶ ይታገል እንላለን፡፡ አምባገነንነት ሲወገድ እውነተኛው ምርጫ በሕዝብ ትግል እውን ይሆናል፡፡

አምባገነን አገዛዝ በሕዝብ ትግል ይወገዳል!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!
ለወያኔ ምርጫ ሳይሆን ለፀረ ወያኔ ትግል እንነሳ!!